በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የህንፃና የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ደረጃና ቁጥጥርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2004 ዓ.ም.

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕሳማ(ተልዕኮ) 3

- ከተሞች ለምርት፣ ለንግድ፣ ለአገልግሎት እና ለነዋሪዎቻቸው ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ እና እንዲያስተዳድሩ ለማስቻል፣ 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር 5

የሰው ኃይል 5

የፋይናንስ ምንጭ 6

የኦዲቱ ዕሳማ 7

የኦዲቱ ትኩረት ዕቀጣጫዎች (Issues) 7

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች 8

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 8

1.2 የአሠራር ፍሰት መግለጫ (Process Description) 9

ክፍል ሁለት 10

ግኝቶች 10

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተዘጋጀው የህንፃ መመሪያ 10

ስለመሰራጨቱ፣ በሰነዱ ላይ ተገቢው ስልጠና 10

(የግንዛቤ ማስጨበጫ) ስለመሰጠቱ እና ስለመተግበሩ፣ 10

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚገኙትን ሰነዶች 11

(ኮዶች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች…) 11

ማግኘት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች በሙሉ የሰነዶቹን ዝርዝር 11

ሲያውቁና ሲያገኙ የሚችሉበት የመረጃ ስርዓት ስለመዘርጋቱ፣ 11

በክልልና ከተማ መስተዳድር በጀትና ድጋፍ ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች ከመገንባታቸው በፊት በቂ የመነሻ ጥናት ስለመደረጉ፣ 12

በህንፃና በመኖሪያ ቤት ግንባታ ወቅት ምን ያህሉ ቦታ ለአረንጓዴ ሽፋን መዋል እንዳለበት የተዘጋጀ መመሪያ ስለመኖሩ፣ 14

ያለ አማካሪ መሀንዲስ ክትትልና ቁጥጥር የሚሰሩ የመኖሪያ ቤቶች እና ሕንፃዎችን በተመለከተ፣ 16

የግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ቦታ የግንባታ ክትትል የመረጃ መዝገብ የሚዘጋጅና በሚገባ የሚሠራበት ስለመሆኑ፣ 18

በግንባታ ሂደት ለግንባታ ግብዓት የሚውል የግብዓት ጥራት የናሙና ፍተሻ ስለመደረጉ፣ 19

የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንፃዎች ግንባታ የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ ታሳቢ ያደረጉ ስለመሆናቸው፣ 21

የመስታወት ግድግዳ የሚገጠምላቸው ህንፃዎች መስታወቱ ደረጃውን የጠበቀና ጉዳት የማያስከትል ስለመሆኑ፣ 22

መሬ ሰነዶች አስገዳጅ፣ ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩና የሚተገበሩ ስለመሆናቸው ፣ 23

በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የደህንነት መጠበቂያዎችን የሚጠቀሙ ስለመሆኑ፣ 25

የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ብዛትና የማጠናቀቂያ ጊዜ በመርሐ ግብር ከተያዘው ጋር የሚጣጣም ስለመሆኑ፣ 27

የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ሥራ ጎን ለጎን የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ስለመከናወኑ፣ 29

በአንድ ቦታ ላይ በርከት ብለው የሚገነቡ ህንጻዎች የዝናብ ውሃ መሰብሰብ የሚችሉ (water harvesting) 31

ሆነው ስለመሠራታቸው፣ 31

ምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ሲገነቡ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና የማምለጫ አመላካቾች ስለመዘጋጀታቸው፣ 32

ክፍል ሦስት 33

የመደምደሚያ ሀሳቦች 33

ክፍል አራት 36

የማሻሻያ ሀሳቦች 36

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
የህንፃና የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ደረጃና ቁጥጥርን በተመለከተ
የክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. ቀደም ሲል የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 471/98 ተቋቁሞ የከተማ ዘርፍ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪንና የመንገድ ዘርፍን የመንግሥት የልማት ቅጣጫን በመከተል ሲመራ፣ ሲያስተባብርና ሲከታተል ነበር፡፡

2. ሆኖም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሠረት ስያሜው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል በአዲስ መልክ ተደራጅቷል፡፡

3. መ/ቤቱ በአዲሱ አደረጃጀት በከተማ ዘርፍና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የተደራጁ መ/ቤቶችን እንዲመራ፣ እንዲያስተባብርና እንዲከታተል ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ የከተማ ልማት ዘርፍን እና የአገራዊ ኮንስትራክሽን አቅም ግንባታን አጣምሮ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ በከተማ ልማት ዘርፍ በዋናነት ብሔራዊ የከተማ ልማት ፖሊሲን፣ የከተሞች የኢንዱስትሪና የከተማ ልማት እና የከተሞች መልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጆችን፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ደግሞ ለዘርፉ ዕድገት የሚያስፈልጉ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማዘጋጀት፣ የአቅም ግንባታ ሥልጠና የመስጠት፣ በዘርፉ የተሰማሩ አገር በቀል የሥራ ተቋራጮች አቅም የሚጠናከርበትን ሥልት የመቀየስና ሌሎችንም ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን ናቸው፡፡

5. ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ባለፉት አመታት 16 በመቶ ወይም 11.7 ሚሊዮን የሚሆነው የሀገሪቱ ሕዝብ የሚኖረው በከተማ ሲሆን የከተማው ነዋሪ ሕዝብ ዓመታዊ የዕድገት ምጣኔም 4.3 በመቶ ወይም በዓመት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ተጨማሪ ሕዝብ እንደሚኖር ይገመታል፡፡ ሀገራችን ከፍተኛ የሆነ የከተማ

ሕዝብ ዕድገት ካላቸው አገሮች አንዷ ስትሆን፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ድህነት በሀገራችን በተለይም በከተሞች እየሰፋ በመምጣቱ ምክንያት የመጠለያ ችግር፣ ሥራ አጥነት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማቶች እጥረት እንዲባባስ አድርጓል፡፡ በዋና ዋና የአገሪቱ ከተሞች ያለው የመጠለያ ችግር ደረጃ የተለያየ ቢሆንም፣ ባለፉት ዓመታት የተካሄዱ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት 70 ከመቶ የሚሆነው የከተማ ነዋሪ የሚኖረው ደረጃቸውን ባልጠበቁና በተጨናነቁ አካባቢዎች ነው፡፡ በአጠቃላይ ደካማ የኢኮኖሚ መሠረት፣ ከፍተኛ ሥራ አጥነትና ድህነት፣ የተጨናነቁ እና መሠረታዊ አገልግሎት ያልተሟላላቸው መኖሪያ ቤቶች የሀገራችን ከተሞች መገለጫዎች ናቸው፡፡

6. በመሆኑም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለመኖሪያ ቤቶች ልማት የጥናትና ምርምር ውጤቶችን፣ ጥራታቸው የተሟሉና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ልዩ ልዩ ዲዛይኖችን፣ የሕንፃ ግንባታ ማስፈፀሚያ ሥርዓት የሚሆኑ መሪ ሰነዶችን በማቅረብ፣ ለባለሙያዎች የክህሎት ማሳደጊያ ስልጠና በመስጠት፣ በሚቀመጡ የጥራት መስፈርቶች መሠረት ቋሚ የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት፣ ለባለሙያዎች፣ ለሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የምዝገባ የምስክር ወረቀትና ለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲኖር የማድረግ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ

7. "ለኑሮ ምቹና ተወዳዳሪ የሆኑ ከተሞች እና ዓለም-አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በ2012 ተፈጥሮ ማየት"፡፡ ይህ ራዕይ በውስጡ የያዛቸው መሠረታዊ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ለኑሮ ምቹና ተወዳዳሪ የሆኑ ከተሞች

ከተሞች ቀልጣፋና ውጤታማ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን እና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ-ልማቶችን ለነዋሪዎች በማቅረብ ለኑሮ ምቹና፣ ተወዳዳሪ ከተሞች እንዲሆኑ እና ቀጣይነት ያለው ዘርፈ ብዙ ልማት ማስተናገድ የሚችሉ የልማት ማዕከላት በመሆን በገጠሩ አካባቢ እየተመዘገበ ያለውን ልማት እንዲደግፉና እንዲያፋጥኑ ብሎም ለአገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት የጎላ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

ዓለም-አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ

ሃገራዊውን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አቅም በተለያዩ ስልቶች የማሳደግ፣ ከዓለም-አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጋራ ተወዳድሮ የአገር ውስጥ የኢንዱስትሪውን ፍላጐት ለማሟላትም ሆነ በውጭ ገበያ ተወዳድሮ የውጭ ምንዛሪ የማምጣት አቅም እንዲኖረው ማስቻልን የሚያመለክት ነው፡፡

<u>የሚኒስቴር መ/ቤቱ አላማ(ተልዕኮ)</u>

8. የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አላማዎች፡-

- የከተሞችንና የክልሎችን የማስፈጸም አቅም በቀጣይነት ለመገንባት የሚያስችል የሰው ኃይል ልማት፣ አደረጃጀትና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለማሻሻል፣
- ሰፊ የሥራ ዕድልን በመፍጠር ድህነትን በማስወገድ ሰፊ መሠረት ያለው ልማታዊ ባለሀብት በመፍጠር፣ ለኢንዱስትሪው ልማት አስተማማኝ መሠረት በመሆን በአገሪቱ ልማት ውስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወት በምርትና በአገልግሎት ተወዳዳሪና ብቁ የሆነ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዘርፍ ለማፍራት፣
- የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥርዓት አፈፃፀም ግልጽ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት፣ ፍትሃዊና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አግባብ እንዲከናወን በማስቻል በከተሞች የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን ለማድረቅና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታን ለመፍጠር፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለሃገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት መፋጠን ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ እና የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ፣
- <u>ከተሞች ለምርት፣ ለንግድ፣ ለአገልግሎት እና ለነዋሪዎቻቸው ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ እና እንዲያስተዳድሩ ለማስቻል፣</u>
- ከተሞች/ማዘጋጃ ቤቶች የመሰረተ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻልና ዕድገታቸውን ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የገቢ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ለማስቻል ነው፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

9. መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 ዓ.ም. የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-

- ✓ አከታተምን በሚመለከት ጥናት ማካሄድ፣ የከተሞችን ደረጃ መመዘኛ ማውጣት፤
- ✓ ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት፤ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ የአቅም ግንባታ እገዛ ማድረግ፤
- ✓ ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ማድረግ፣ ተግባራዊ እንዲሆን ማገዝና አፈጻጸሙን መከታተል፤
- ✓ ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ የከተማ አስተዳደሮችን የሥራ እንቅስቃሴዎች መከታተል፤
- ✓ የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ መኖሪያ ቤት እንዲሠራ አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ለተግባራዊነታቸውም ለከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ፤
- ✓ ለሌሎች አካላት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ለኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች ማውጣትና መከበራቸውን መከታተል፤ ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ፤
- ✓ በፌዴራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎቹን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፤
- ✓ መሐንዲሶችንና አርክቴክቶችን መመዝገብ፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፣ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ መወሰን፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፤
- ✓ በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ማካሄድ፤

- ✓ በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶች አስተዳደር በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ማረጋገጥ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሆኖ በአንድ ሚኒስትርና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ይመራል፡፡ አደረጃጀቱም 1 የኦዲት መምሪያና 11 ቢሮዎች ያሉት ሲሆን፣ እነርሱም የሚኒስትር ጽ/ቤት እና የሚኒ ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ (በሥሩ የሕግ ክፍልን ይዟል)፣ የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ፣ የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ፣ የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ግንባታ ቢሮ፣ የከተማ ፕላን ጽዳትና ውበት ቢሮ፣ የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ፣ የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ (በሥሩ ፋይናንስን ይዟል) እና የኢንተርፕራይዞች ልማትና የመንግሥት ቤቶች አስተዳደር ክትትልና ድጋፍ ጽ/ቤት ናቸው፡፡

11. ጥቅምት 1/1998 ዓ.ም. በወጣው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 33/7 መሠረት የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑ አካላት ሲሆኑ፣ መስከረም ወር 2003 ዓ.ም በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ልማት ኤጀንሲ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የሰው ኃይል

12. በሰኔ 2003 ዓ.ም. አዲስ በፀደቀው መዋቅር መሠረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደው የሥራ መደብ 578 ሲሆን በታህሣስ ወር 2004 ዓ.ም. በሥራ ላይ ያለው የሰው ሀይል ወንድ 245 ሴት 102 በአጠቃላይ 347 ቋሚ ሠራተኞች አሉት፡፡

13. ከላይ ከተጠቀሱት ቢሮዎች መካከል በኦዲቱ የታዩት የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ግንባታ ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ ናቸው፡፡

14. የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ግንባታ ቢሮ በሥሩ ሁለት የሥራ ሂደቶች ያሉት ሲሆን እነሱም የመኖሪያ ቤቶች ልማት ክትትልና ድጋፍ ዋና የሥራ ሂደት ምክትል ቢሮ እና የመንግስት ሕንፃዎች ኮንስትራክሽን ክትትልና ድጋፍ ዋና የሥራ ሂደት ምክትል ቢሮ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ለቢሮው በመዋቅር የተፈቀደው የሥራ መደብ 65 ሲሆን፣ በታህሣስ ወር 2004 ዓ.ም. 31 ቋሚ ሠራተኞች ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡

15. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ በበኩሉ አራት የሥራ ሂደት ሲኖሩት፣ እነሱም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል ልማትና የደረጃዎች ዝግጅት የሥራ ሂደት፣ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ባለሙያዎችና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባ የሥራ ሂደት፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሕግ ማስፈፀም የሥራ ሂደት እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ግብዓት እና ቴክኖሎጂ ምርምር የሥራ ሂደት ናቸው። ቢሮዉ በአጠቃላይ 53 ሠራተኞች እንዲኖረው የተፈቀደ መዋቅር ሲኖረው፣ በታህሣስ ወር 2004 ዓ.ም. 44 ቋሚ ሠራተኛ ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የፋይናንስ ምንጭ</u>

16. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢ ምንጭ ከመንግሥት የሚመደብ በጀት፣ ከውጭ የሚገኝ ዕርዳታ እና ከውጭ የሚገኝ ብድር ናቸው፡፡

17. በ2000 በጀት ዓመት ለመደበኛ ብር 16.7 ሚሊዮን፣ ለካፒታል ብር 85 ሚሊዮን እና በጠቅላላው ብር 101.8 ሚሊዮን የተመደበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ ብር 13.8 ሚሊዮን እና ለካፒታል ብር 38.3 ሚሊዮን በድምሩ ብር 52.1 ሚሊዮን ወጪ ሆኗል:: በ2001 በጀት ዓመት ደግሞ ለመደበኛ ብር 24.6 ሚሊዮን እና ለካፒታል ብር 241.4 ሚሊዮን (ከዚህ ውስጥ ብር 75.3 ሚሊዮን ከውጭ ዕርዳታ የተገኘ) በጠቅላላው ብር 266 ሚሊዮን የተመደበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ ብር 17.7 ሚሊዮን እና ለካፒታል ብር 241 ሚሊዮን በድምሩ ብር 258.7 ሚሊዮን ወጪ ተደርጓል፡፡

18. በ2002 በጀት ዓመት ለመደበኛ ብር 23.3 ሚሊዮን እና ለካፒታል ብር 215.4 ሚሊዮን (ከዚህ ውስጥ ብር 80 ሺ ከውጭ ዕርዳታ የተገኘ) በጠቅላላው ብር 238.7

ሚሊዮን የተመደበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ ብር 17.9 ሚሊዮን እና ለካፒታል ብር 181 ሚሊዮን በድምሩ ብር 199 ሚሊዮን ወጪ ሆኗል፡፡

19. በ2003 በጀት ዓመት ለመደበኛ ብር 23.9 ሚሊዮን እና ለካፒታል ብር 324.9 (ከዚህ ውስጥ ብር 75 ሚሊዮን ከውጭ ዕርዳታ የተገኘ) በጠቅላላው ብር 348.8 ሚሊዮን የተመደበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከሐምሌ 2002 እስከ የካቲት 2003 ባለው የ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ለመደበኛ ብር 11.2 ሚሊዮን እና ለካፒታል ብር 101.1 ሚሊዮን በድምሩ ብር 112.3 ሚሊዮን ወጪ ሆኗል፡፡

የኦዲቱ አላማ

20. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከተቋቋመበት አላማ አንፃር የጥራት ደረጃውን የጠበቀና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን ለማሳደግ፣ ነዋሪዎች ሊገዙ የሚችሉትን የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ቤት ለመስራት፣ ጠንካራ ቅንጅታዊ አሠራርና የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ለማስፈፀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መኖሩን በማጣራት ችግሮችን በመለየትና የማሻሻያ ሀሳብ በመስጠት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አሠራር እንዲኖረው እና ሕብረተሰቡም ተጠቃሚ እንዲሆን እገዛ ለማድረግና የመሥሪያ ቤታችንን የክዋኔ ኦዲት ዓላማም ለማሳካት ነው፡፡

የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫዎች (Issues)

21. ከላይ የተመለከተውን የኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት፣ በህንፃና መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ደረጃና ቁጥጥር ላይ ሊከናወን ለታቀደው የክዋኔ ኦዲት ሦስት የትኩረት አቅጣጫዎች ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም:-

- ኮዶች፣ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች ስለመኖራቸው፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ስለመከናወናቸው፣ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ስለመዳረሳቸውና ስለመተግበራቸው ማጣራት፣
- በፌዴራል መንግስት በጀትና ድጋፍ በፌዴራልና በክልል ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች የመነሻ ጥናት መኖሩን፣ ግንባታውም ደረጃውን የጠበቀ

እንዲሆን ተገቢው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን፣ የስራ ክንውኑም በተያዘለት ጊዜና የገንዘብ መጠን መሆኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን ማጣራት፣

➢ ከመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፣ የመረጃ ባንክ መኖሩንና የአያያዝና የጥንቅር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ማጣራት፣

ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

22. ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት የትኩረት አቅጣጫዎች ኦዲት ለማድረግ እንዲያስችል በድምሩ 53 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎችና መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ አንድ ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

23. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ በክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው በዋነኛነት በከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መ/ቤት ሲሆን፣ ኦዲቱን ለማከናወን ከ2001-2003 በጀት ዓመት የተከናወኑ ሥራዎችን የሚገልጹ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ፣ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለሚገኙ ኃላፊዎች፣ ለኢትዮጵያ አማካሪ መሐንዲሶችና አርክቴክቶች ማህበር ኘሬዝዳንትና ፀሐፊ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሲቪል መሐንዲሶች ማህበር ኘሬዝዳንት ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ነው፡፡

24. በተጨማሪም የኦዲቱ ሥራ ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ኦዲተሮች በተጨማሪ በዘርፉ ለኦዲቱ ሥራ የቴክኒክ እገዛ የሚያደርግ ባለሙያ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማህበር በተጠየቀው መሰረት ማህበሩ መርጦ በላከው አማካሪ መሀንዲስ የባለሙያ እገዛ ተደርጓል። የተመደቡት ባለሙያም

ከኦዲት ቡድኑ ጋር በመሆን በናሙና በተመረጡ በአዲስ አበባ ለአራዳ ክፍለ ከተማና ለአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ በክልል ከተሞች በኦሮሚያ አዳማና ሻሸመኔ፣ በደቡብ አዋሳና ይርጋለም፣ በአማራ ባህር ዳር ለማዘጋጃ ቤቶችና ለቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎች እንዲሁም ለአዋሳ ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር ባለሥልጣን ኃላፊ፣ ለባህር ዳር ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ ከእነርሱ የተገኘን መረጃ በመከለስ፣ እንዲሁም በናሙና በተመረጡ በአዲስ አበባ ኮልፌ ቀራንዮ፣ ቦሌና የካ ክፍለ ከተሞች እና ከላይ በተጠቀሱ የክልል ከተሞች የግንባታ ቦታ ተገኝቶ በማየትና አስፈላጊ መረጃዎችን በመከለስ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

25. በዚህ መሰረት አንዳንድ በኦዲት ሪፖርቱ ውስጥ የተቀመጡ ግኝቶች፣ መደምደሚያዎችና የማሻሻያ ሀሳቦች በቀጥታ ሚኒስቴር መ/ቤቱን ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆኑ የተለያዩ በህንፃና በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ላይ የተሰማሩ የፌዴራልና የክልል ከተሞች አስፈፃሚ አካላትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለሁሉም መ/ቤቶች የሪፖርት ቅጂዎች ለመላክ ከጊዜና ከአሰራር ግንኙነት አንጻር የተመቸ ባለመሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ካለው የሥራ ግንኙነት አንፃር ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሁሉ የሪፖርቱን መልዕክት እንዲያስተላልፍ እንጠይቃለን፡፡

1.2 የአሠራር ፍሰት መግለጫ (Process Description)

26. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ ሥር ለሚገኙ አራት ንዑስ የሥራ ሂደቶች ማለትም ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሰው ሃይል ልማት እና የደረጃዎች ዝግጅት የሥራ ሂደት፣ ለስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ባለሙያዎች እና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ የስራ ሂደት፣ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሕግ ማስፈፀም የሥራ ሂደት፣ ለኮንስትራክሽን ግብዓትና ቴክኖሎጂ ምርምር የሥራ ሂደት እንዲሁም በመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግሥት ህንፃዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ ሥር ለሚገኙ ሁለት ንዑስ የሥራ ሂደቶች ማለትም ለመኖሪያ ቤቶች ልማት ክትትልና ድጋፍ የስራ ሂደት እና ለመንግስት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ክትትልና ድጋፍ የስራ ሂደት የአሠራር ፍሰት መግለጫ የተዘጋጀላቸዉ ሲሆን፣ እነዚህ መግለጫዎች በዚሁ ሪፖርት መጨረሻ ላይ በአባሪ ሁለት ተያይዘዋል፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተዘጋጀው የህንፃ መመሪያ

ስለመሰራጨቱ፣ በሰነዱ ላይ ተገቢው ስልጠና

(የግንዛቤ ማስጨበጫ) ስለመሰጠቱ እና ስለመተግበሩ፣

27. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚመራባቸውና ለመኖሪያ ቤትና ህንፃ ግንባታ ሥራ አፈፃፀም መለኪያ የሚሆን የህንፃ መመሪያ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሊዘጋጅ፣ የሠነዱ ትግበራ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥና የተሟላ እንዲሆን ለማስቻል ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ለሥራ ተቋራጮች፣ ለአማካሪዎች፣ ለባለሙያዎችና ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊሰጥ፣ ሊያሰራጭና አተገባበሩ ላይም የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

28. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በግንቦት ወር 2003 ዓ.ም ተዘጋጅቶ የፀደቀው የህንፃ መመሪያ ቢኖርም በናሙና በታዩት አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ባህር ዳርና ሀዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች፣ የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ እና የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ባለሥልጣን ኃላፊዎች በሠነዶቹ ላይ የወሰዱትን የግንዛቤ ማስጨበጫ ከታች በሥራቸው ላሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ያላስተላለፉ መሆኑ ታውቋል፡፡

29. እንደዚሁም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያዘጋጀው የህንፃ መመሪያ በናሙና በታዩት በአዳማ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት ጽ/ቤትና በይርጋለም ከተማ ማዘጋጃ ቤት ያልደረሰ መሆኑን፣ እንዲሁም በሻሸመኔና በአዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ሠነዱ ቢደርሳቸውም ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ አለመቅረቡን ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡

30. ሠነዱ የደረሳቸው የይርጋለም፣ የሀዋሳና የሻሸመኔ ከተማ የቤቶች ልማት ኘሮጀክት ጽ/ቤቶች እና የሻሸመኔና አዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች እስከ አሁን ወደ ትግበራ ያልገቡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

31. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የተዘጋጀው የህንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በሀርድ እና በሶፍት ኮፒ መላኩን፣ ያልተላኩባቸውም ክልሎች ክፍተታቸው እንዲሞላ የመጠየቅ ኃላፊነት የክልሎች ቢሆንም፣ ክፍተቱን

አጥርተው ለመሙላት እንደሚከታተሉ፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትም በትርጉም ሂደት ላይ መሆኑን ማረጋገጣቸውንና በአሁኑ ወቅት ለአማራ፣ ኦሮሚያ እና ትግራይ ክልሎች ለሁሉም አመራሮች ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መሰጠቱን፤ እንዲሁም በቀጥታ ለሚመለከታቸው ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ሥልጠና በመስጠት የማጠናከር ሥራዎች እንደሚከናወኑ፣ ሥርጭቱ የደረሳቸውም ወደ ትግበራ ያልገቡት የአደረጃጀትና የህንፃ ሹም ምደባ በአፈጻጸም ሥራ ላይ መሆኑንና አፈጻጸሙን እንደሚከታተሉ ገልጸዋል፡፡

32. ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለሚመለከታቸው ሁሉ ሰነዱን ያሰራጩ መሆኑን ቢገልጹም፣ አንዳንዶቹ ያልደረሳቸውና ከደረሳቸውም አንዳንዶቹ ከክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም መሆኑን የገለጹ ሲሆን፣ የግንዛቤ ማስጨበጫውም ለሦስት ክልሎች ብቻ የተሰጠ ከመሆኑ እና ግንዛቤውን ያገኙት የአመራር አካላትም ወደ ታች አለማውረዳቸው እንዲሁም በፍጥነት ወደ ትግበራ አለመግባቱ የመረጃ ክፍተት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የህንጻ መመሪያውን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫውን የወሰዱ የአመራር አካላት ወደታች አለማውረዳቸው፣ ሰነዱ በሁሉም ቦታ አለመሰራጨቱና መመሪያው ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትል አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚገኙትን ሰነዶች (ኮዶች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች…) ማግኘት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች በሙሉ የሰነዶቹን ዝርዝር ሊያውቁና ሊያገኙ የሚችሉበት የመረጃ ስርዓት ስለመዘርጋቱ፣</u>

33. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚገኙ ሰነዶችን (ኮዶች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች…) ተጠቃሚዎች በሙሉ (የመኖሪያ ቤትም ሆነ ህንጻ የሚገነቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች) በቀላሉ ሊያውቁና ሊያገኙ የሚችሉበት የመረጃ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል::

34. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙትን ሠነዶች ዝርዝር የሚገልጽ መረጃና ሠነዶቹን ማግኘት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች በቀላሉ ሊያገኙ

የሚችሉበት የመረጃ ሥርዓት በበቂ ሁኔታ አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡ በድህረ-ገጽ መጠቀም ለሚችሉ ተጠቃሚዎችም ቢሆን፣ የሁሉም ሰነዶች ዝርዝር በድህረ-ገጹ ላይ ተካቶ አልተገኘም፡፡

35. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙት ሰነዶች ዝርዝር መረጃ በህግ መምሪያ ክትትል እየተደረገ እየወጣ እንደሚገኝ፣ ከዚህ በፊት የወጡትንም ጭምር የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እየከተናወነ እንደሆነ፣ በቀጣይ በኤሌክትሮኒክስ ኮፒ እንደሚዘጋጁና በሽያጭ የሚቀርቡትን ልዩ ልዩ ሰነዶች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ የአቅጣጫ ጠቋሚና የቢሮ ቁጥር አድራሻ መግለጫ በቋሚነት እንደተዘጋጀ እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድህረ-ገፅም የተወሰኑ መረጃዎችን እንዲይዝ መደረጉን እና (በክፍያ የሚወሰዱት ካልሆነ በስተቀር) የሚቀሩትንም አከታትለው እንዲጫን እንደሚያደርጉና የዲዛይን ኮዶችን ተደራሽ ለማድረግ ለክልሎች ከክፍያ ነጻ እንዲዳረስ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

36. ሆኖም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እየተሠራ ያለው ጅምር ሥራ ጥሩ ቢሆንም፣ የተዘጋጁትን ሠነዶች በሙሉ ዝርዝራቸውን የሚገልጽ መረጃ አለመኖሩና ሠነዶቹን ማግኘት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ሁሉንም ሠነዶች በቀላሉ ሊያገኙ አለመቻላቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>በክልልና ከተማ መስተዳድር በጀትና ድጋፍ ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች ከመገንባታቸው በፊት በቂ የመነሻ ጥናት ስለመደረጉ፣</u>

37. በክልልና ከተማ መስተዳድር በጀትና ድጋፍ የሚገነቡ መኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች ከመገንባታቸው በፊት በቂ የመነሻ ጥናት ሊኖራቸው ይገባል።

38. ይሁንና በቂ የመነሻ ጥናት ባለመደረጉ፡-

1. በይርጋለም አቦስቶ አካባቢ የ2000 ዓ.ም. የጋራ መኖሪያ ቤቶች የሚገዛቸው ባለመገኘቱ 12 ብሎኮች ግንባታቸው ባለበት ደረጃ እንዲሸጡ መወሰኑን፣
2. በአዳማ ከተማ የ2000 ዓ.ም ግንባታ ደምበላ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤት ከግንባታው ጀርባ የከተማው የጎርፍ ውሃ ሲያልፍ የመሬት መንሸራተት በማስከተሉ ምክንያት

4ቱ ቆርቆሮ ተመቶ፣ 3ቱ ቆርቆሮ ሳይመታላቸው 4ቱ ደግሞ G+3 ላይ ደርሰው የቆሙ መሆኑን፣

ፎቶ 1 በአዳማ ከተማ በመሬት መንሸራተት ምክንያት ሥራው የተቋረጠው 11 ብሎክ የ2000 ዓ.ም ግንባታ ደምበላ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤት

3. በባህር ዳር የ1999 ሲቪል ሰርቪስ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሁለት ብሎኮች መሠረት ከወጣ በኋላ ቦታው ላይ ውሃ በመፍለቁ ምክንያት ሥራው መቋረጡን፣

ፎቶ 2 መሰረት ከወጣ በኋላ ውሃ ፈልቆበት ሥራው የተቋረጠው የባህር ዳር የ1999 ሲቪል ሰርቪስ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤት

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በጋራ መኖሪያ ቤቶች ላይ የታዩት ችግሮች ትክክል እንደሆኑና በይርጋለም በ2000 ዓ.ም. የተገነቡ የጋራ መጠቀሚያ ቤቶች ገዢ ስላጡ ባሉበት ደረጃ እንዲተላለፉ በመንግስት ተወስኖ አፈጻጸሙ ክትትል እየተደረገበት እንደሆነና፣ በአዳማና በባህር ዳር ሳይንሳዊ መፍትሄ ለመስጠት ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

44. ይሁን እንጂ በክልልና በከተማ መስተዳድሮች በቂ ጥናት ሳይደረግ የጋራ መኖሪያ ቤቶቹ በመገንባታቸው ምክንያት ከላይ የተመለከቱት ችግሮች በመከሰታቸው ፕሮጀክቶቹ በዕቅድ በታያዘላቸው ጊዜ፣ ዋጋና ብዛት እንዳይጠናቀቁና በወቅቱ ለታለመላቸው አላማ እንዳይውሉ ሆነዋል፡፡

በህንፃና በመኖሪያ ቤት ግንባታ ወቅት ምን ያህሉ ቦታ ለአረንጓዴ ሽፋን መዋል እንዳለበት የተዘጋጀ መመሪያ ስለመኖሩ፣

45. ለመኖሪያ ቤትም ሆነ ለህንፃ ግንባታ በተፈቀደ ቦታ ላይ ለአረንጓዴ ሽፋን ለሚውል ስፍራ እንደየከተሞቹ ነባራዊ ሁኔታ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት:: ለተፈፃሚነቱም የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

46. ይሁንና በመንግስትም ሆነ በግለሰብ ለሚገነቡ ህንፃዎች ወይም መኖሪያ ቤቶች ለግንባታ ከተፈቀደላቸው ቦታ ምን ያህሉን ለአረንጓዴ ሽፋን መጠቀም እንደሚገባቸው የሚገልፅ መመሪያ በናሙና በታዩ ከተሞች አልተዘጋጀም፡፡

47. በኦዲቱ ወቅትም በናሙና በተመረጡ የግንባታ ቦታዎች በመገኘት በተደረገው ማጣራት፣ በሀዋሳ ከተማ በማዘጋጃ ቤት ቁጥጥር የሚሠራው የግለሰብ ሴንትራል ሆቴል ለአረንጓዴ ሽፋን የሚሆን ቦታ በዲዛይኑ ላይ እንደተቀመጠ፣ ነገር ግን በግንባታው ወቅት እንዳልተተገበረ እና በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ታረቅ ሳብት ሆቴል፣ በአዳማ የንግድ ሥልጠና ማዕከል /BIC/ እና ማይክሮ ክላስተር፣ በሀዋሳ ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር ባለሥልጣን በሚሰሩ የኤች.አይ.ቪ ሪሶርስ ቢሮ G+5 ግንባታቸው የአረንጓዴ ሽፋን የሌለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

48. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የተለያዩ አካላት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- የኢትዮጵያ አማካሪ መሐንዲሶችና አርክቴክቶች ማህበር ፕሬዘዳንትና ፀሐፊ ዲዛይን ሲሰራ የአረንጓዴ ሽፋን መኖሩ ታይቶ እንዲፀድቅ ቢደረግም፣ ወደ ሥራው ሲገባ ግን ቦታ እንደማባከን እንደሚቆጠርና ግንዛቤውም እንደሌለ፣ ከግቢ ውጭ ላለውም ቢሆን፣ ለአረንጓዴ ሽፋን በመንግስት ትኩረት እንዳልተሰጠውና ህግም እንዳልወጣለት ገልጸዋል፡፡
- የኢትዮጵያ ሲቪል መሐንዲሶች ማህበር ፕሬዝዳንት፣ በአዲስ አበባ የአረንጓዴ ሽፋን እንዲኖር ለማድረግ ለአረንጓዴ ሽፋን ተብሎ የሚሰጥ ቦታ እንደሌለ፣ ህብረተሰቡም ለአረንጓዴ ሽፋን ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑንና ለአረንጓዴ ሽፋን የሚተው ቦታዎችን ማህበረሰቡ ሌላ ነገር እንዳይሰራበት ህግም መውጣት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡
- በናሙና ተመርጠው በታዩ የየከተሞቹ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች ሲገልጹ፡-
  - በአዲስ አበባ ከተማ ለጋራ መኖሪያ ቤቶች በ1999 ከተገነቡ ሳይቶች በተሻለ የ2000 ግንባታ ለአረንጓዴ ሽፋን የተተወ ቦታ እንዳለና ሌላው ከሥራ ተቋራጩ ጋር ባለ ውል መሰረት አንድ ብሎክ የሚሰራ ሥራ ተቋራጭ ሁለት ዛፍ እንዲተክል እንደሚደረግ፣
  - በሻሸመኔ በቂ የአረንጓዴ ሥፍራ እንዳለው፣
  - በአዋሳና በአዳማ የ1999 ዓ.ም. ግንባታ በቂ የአረንጓዴ ሽፋን ቦታ የሌለውና የ2000ው ግን በቂ ቦታ እንዳለው ገልጸዋል፡፡
- በይርጋለም ግንባታ የሚያከናውኑ ባለሀብቶች በግንባታቸው ቦታ የአረንጓዴ ሽፋን ቦታ እንዲተው እንደማይገደዱና በዲዛይኑ ላይ እንዲታይም እንደማይደረግ፣ በሀዋሳ ዲዛይን ሲሰራ ለአረንጓዴ ሽፋን የሚሆን ቦታ እንዲኖረው የሚያስገድድ መመሪያ እንደሌለ፣ በሻሸመኔ በአጠቃላይ የቦታ እጥረት በመኖሩ በቂ የአረንጓዴ ቦታ ይኑር ብለው ለማስገደድ እንደሚቸገሩ፣ በአዳማና በባህር ዳር ዲዛይን ሲጸድቅ የአረንጓዴ ቦታ ሳይታይ እንደማይጸድቅና ነገር ግን በጸደቀው መሰረት መሠራቱን መከታተሉ ላይ ችግር እንዳለ የየከተሞቹ ማዘጋጃ ቤት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

49. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ለሁሉም ወጥ የሆነ መመሪያ ሊዘጋጅ እንደማይችልና እንደየከተሞቹ ባህሪ እንደሚለያይ ገልጸዋል፡፡

50. ሆኖም ከላይ እንደተመለከተው ሁሉም የግንባታ ባለቤቶች የአረንጓዴ ሽፋንን በተመለከተ የሚያመቻቸውን እንደሚያደርጉና ለጉዳዩ ብዙ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ ታውቋል፡፡ ስለሆነም ኃላፊዎቹ እንደገለጹት ወጥ የሆነ መመሪያ ማዘጋጀት ባይቻልም፣ እንደየከተሞቹ ነባራዊ ሁኔታ ተጠንቶ በስትራቴጂክ እንዲደገፍ ለማድረግ ቢታሰብበት መልካም ነው፡፡

ያለ አማካሪ መሀንዲስ ክትትልና ቁጥጥር የሚሰሩ የመኖሪያ ቤቶች እና ሕንፃዎችን በተመለከተ፣

51. በግንባታ አማካሪዎች ክትትልና ቁጥጥር መሰራት ስላለባቸው የመኖሪያ ቤቶች እና ሕንፃዎች ደረጃ ለይቶ የሚያሳይ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ፣ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን ለማጣራት በናሙና በታዩ ከተሞች፡-

- በአዲስ አበባ ከጥር 15/2001 ዓ.ም በፊት ያሉ የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታዎች ያለአማካሪ ባለሙያ ተሳትፎ ቀጥታ ከሥራ ተቋራጩ ጋር ባለው ውለታ ሲሰሩ የነበረ መሆኑን፣
- በሀዋሳ፣ በባህር ዳርና በአዳማ የ1999 ግንባታዎች ያለአማካሪ ተሳትፎ እንደተሰሩ፣ በሻሸመኔና በይርጋለም አማካሪ ባለሙያዎች የመስክ ጉብኝት እስከተደረገበት ጊዜ በግንባታው ሂደት ተሳትፈው እንደማያውቁ፣

በየከተሞቹ የሚገኙ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

ፎቶ 3 ያለአማካሪ ተሳትፎ እየተገነባ ያለ የሻሸመኔ ከተማ የ2000 የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ

53. እንደዚሁም በግንባታ ቦታ በመገኘት የታዩት በሻሸመኔ ቤኬራ ኃ/የተ/የንግድ ማህበር G+6፣ በይርጋለም ወኢማ ሪል እስቴት G+3፣ በሀዋሳ ሴንትራል ሆቴል G+8፣ በባህር ዳር ወይዘሮ አስራት ህንፃ G+4 የግለሰብ ህንፃዎች የግንባታቸው ሂደት የአማካሪ ተሳትፎ የሌለበት መሆኑ ታውቋል፡፡

ፎቶ 4 ያለአማካሪ ተሳትፎ እየተገነባ ያለው በአዋሳ ከተማ የሚገኝ የግለሰብ ህንፃ (ሴንትራል ሆቴል)

54. ስለሁኔታው የየከተሞቹ ማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅና የባህር ዳር ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአዳማ የህንፃ ግንባታን በራሳቸው ባለሙያ እንደሚከታተሉ፣ በባህር ዳር በግንባታ ሂደት ላይ ያለው የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ደካማ መሆኑን የግንባታ ህግ በሚተላለፉ አካላት ላይ እንኳን የሚወሰድ እርምጃ እንደሌለና ክህሎት ያለው ባለሙያ (ሥራ ተቋራጭ) የማይሳተፍባቸው ግንባታዎች እንዳሉ፣ በሻሸመኔ የሚሰሩ ትልልቅ ግንባታዎች ያለ አማካሪ እንደሚሰሩና በአዋሳ ያለአማካሪ መሥራት እንደሌለባቸው የሚያሳይ መመሪያ

ካለመኖሩም በላይ አማካሪ ባለሙያም ስለሌለ ያለአማካሪ የሚገነቡ ህንፃዎች እንዳሉና በተለይ በግል የሚሰሩ ግንባታዎች ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ክትትል እንደማይደረግባቸውና በራሳቸው መሀንዲሶች እንደሚቆጣጠሩ፣ እንዲሁም በይርጋለም ለጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ከክልሉ የሚመጡ አማካሪዎች በተወሰነ ጊዜ ከመምጣትና በከተማው ለሚገኙ መኖሪያ ቤት ግንባታዎች በማዘጋጃ ቤቱ ባሉ መሀንዲሶች ክትትል ከማድረግ ውጪ ግንባታውን የሚያከናውነው አካል አማካሪ መሀንዲስ እንደሌለው ገልጸዋል፡፡

55. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ያለአማካሪ መሀንዲሶች ተሳትፎ እንዳልተከናወኑ የግል ዘርፉንም በተመለከተ የተደራጀ የአማካሪ ድርጅት ክትትልና ተሳትፎ ባይደረግበትም፣ በየማዘጋጃ ቤቱ የግንባታና ዲዛይን ባለሙያዎች እንዲሁም ባለሀብቶች በሚቀጥሯቸው ባለሙያዎች ክትትል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

56. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በቃለመጠይቅና በቦታው በመገኘት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ እንደተቻለው፣ ያለአማካሪ ተሳትፎ የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች መኖራቸውን፣ የግለሰብ ህንፃዎችም በማዘጋጃ ቤቱ ግንባታና ዲዛይን ባለሙያዎች የሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር በሰው ኃይል እጥረት የተነሳ በቂ እንዳልሆነና አማካሪ የማይቀጥሩ ባለሀብቶችም እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ስለሆነም በባለሙያ በቂ ክትትልና ቁጥጥር ያልተሠራ ግንባታ የጥራት ደረጃውን የማይጠብቅ በመሆኑ ያለአማካሪ ተሳትፎ መገንባቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>የግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ቦታ የግንባታ ክትትል የመረጃ መዝገብ የሚዘጋጅና በሚገባ የሚሠራበት ስለመሆኑ፣</u>

58. ግንባታ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው የግንባታ ሥራ በሚያከናወንበት ቦታ የግንባታ ክትትል የመረጃ መዝገብ (site book) ሊያዘጋጅ እና የግንባታ ተቆጣጣሪውም ክትትል በሚያደርግበት ወቅት ያገኘውን መረጃ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ ሊያሰፍር ይገባል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት በግንባታ ቦታ ላይ በመገኘት በናሙና በታዩት በይርጋለም ወኢማ ሪል ስቴት የገበያ አዳራሽ G+3፣ በሻሸመኔ ቤኬራ የንግድ ማዕከል G+6፣ በሀዋሳ ኦሞ

ማይክሮ ፋይናንስ G+6፣ የግለሰብ ሴንትራል ሆቴል G+8 እና የማዘጋጃ ቤቱ የስብሰባ አዳራሽ እንዲሁም በባህር ዳር ወይዘሮ አስራት ህንፃ G+4 በግንባታው ቦታ የመረጃ መዝገብ (site book) አልተገኘም፡፡

60. በተጨማሪም በመንግስትና በግለሰብ ህንጻዎች በሻሸመኔ አልፎ አልፎ የመረጃ መዝገብ እንደሚቀመጥ፣ ሆኖም ሳይት ላይ የታየውን ሁኔታ እና የተወሰደውን እርምጃ ቢሮ በተቀመጠው መዝገብ ላይ የማስፈር አሰራር እንዳለ፣ በባህር ዳር በግለሰብ የግንባታ ቦታ የመረጃ መዝገብ እንደማይቀመጥና በአዳማ የመረጃ መዝገብ እንዳለና ነገር ግን የአካሄድ ችግር እንዳለ የየከተሞቹ የማዘጋጃ ቤት ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡

61. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፣ የህንጻ አዋጁን ተከትሎ የግንባታ የመረጃ መዝገብ አደራጃጀት ባለመጠናቀቁ ሊሟላ የማይችል ቢሆንም፣ በዚህ ጥቆማ መነሻ ጉዳዩን እንደሚከታተሉ ገልጸዋል፡፡

62. በመሆኑም ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች ለመረዳት እንደተቻለው በብዙዎቹ የመንግስትና የግለሰብ ህንጻዎች ላይ የመረጃ መዝገብ የማይቀመጥ መሆኑ ታውቋል:: ይህ ደግሞ በግንባታ ወቅት የታዩ ችግሮችንና ልዩ ልዩ ትእዛዞችን አማካሪው ለሥራ ተቋራጩ የሚገልጽበትና የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን የሚያረጋግጥበት በመሆኑ፣ የመረጃ መዝገብ (site book) አለመኖሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>በግንባታ ሂደት ለግንባታ ግብዓት የሚውል የግብዓት ጥራት የናሙና ፍተሻ ስለመደረጉ፣</u>

63. ማንኛውም ግንባታ በግንባታ ሂደት ላይ እያለ በየደረጃው የግብዓት ጥራት የናሙና ፍተሻ ሊደረግና ውጤቱ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ ማህተም ሰፍሮበት ሊቀርብ ይገባል::

64. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት ለግንባታ ለሚውሉ ግብዓቶች መደረግ ስላለበት የናሙና ምርመራ ዝርዝር መመሪያ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተዘጋጅቶ አልተሰራጨም::

65. በናሙና በተመረጡ የግንባታ ቦታዎች፣ ማለትም በአዲስ አበባ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቁጥጥር ሥር የተገነባው ወረዳ 14 የድል ፍሬ ጤና ጣቢያና በመገንባት ላይ ያለው ወረዳ 13 ጤና ጣቢያ እንዲሁም በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ጤና ጣቢያ፣ በባህር ዳር የ1999 ዓ.ም ሳይት ሰባት እና የ2000 ዓ.ም ማሪያም ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣

በሀዋሳ በማዘጋጃ ቤት ቁጥጥር በሚሰራው የስብሰባ አዳራሽና በዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር ባለሥልጣን በሚሰራው ኤች.አይ.ቪ. ሪሶርስ ማዕከል፣ በይርጋዓለም ወኢ.ማ ሪል ስቴት፣ በሻሸመኔ ቤኬራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበርና በአዳማ ማዘጋጃ ቤት ቁጥጥር የሚሰራው ማይክሮ ክላስተርና የንግድ ሥልጠና ማዕከል /BIC/ በመገኘት በግንባታ ሂደት ሊደረግ የሚገባው የግንባታ ግብዓት የናሙና ፍተሻ ያልተደረገባቸው መሆኑን ለማጣራት ተችሏል፡፡

66. ስለጉዳዩ በናሙና በተመረጡ ከተሞች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-
   - በሻሸመኔ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የግብዓት ናሙና ምርመራዎች እንደማይደረጉ፣
   - በባህር ዳር የቤቶች ልማት ኤጀንሲ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ላይ የመስክ የናሙና ፍተሻ እንጂ ስጋት ካልኖረ በስተቀር ምርመራዎች እንደማይደረጉና
   - በአዋሳ ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር ባለስልጣን ግብዓቱ ሲታይ ጥራቱን ያልጠበቀ ከመሰላቸው ፍተሻ እንዲደረግ በደብዳቤ እንደሚያዙ

   ለመረዳት ተችሏል፡፡

67. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፣ በአዲስ አበባ የሚገኘውን የግንባታው አጠቃላይ አፈፃፀም ሪፖርት ስለማይታወቅ ከመስተዳደሩ ጋር ተነጋግረው እንደሚያስተካክሉ፣ የክልሎችን ደግሞ መረጃውን ለክልሉ በመስጠት እንዲጣራ እንደሚያደርጉና ጥቆማውን እንደ ገንቢ ሐሳብ ወስደው ተገቢውን ክትትል አጠናክረው እንደሚቀጥሉ እንዲሁም ከዚህ ቀደም ያለውን አሠራር ለመፈተሽ እንደ ጥሩ አጋጣሚ እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡

68. በመሆኑም በግንባታ ሂደት ለግንባታ ለሚውሉ ግብዓቶች መደረግ ያለበት የናሙና ምርመራ የማይደረግባቸው ግንባታዎች መኖራቸውና ለዚህም በሚመለከታቸው አካላት በቂ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንፃዎች ግንባታ የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ ታሳቢ ያደረጉ ስለመሆናቸው፣

69. የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንፃዎች ሲገነቡ ለአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴ የሚያመቹ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል::

70. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በአዲስ አበባ ከተማ መስተደድር የአራዳ ክፍለ ከተማ የሚገነባቸው፣ በሰሚት ያሉ የ2000 ግንባታ፣ በይርጋዓለም 04 ሳይት፣ የአዋሳ 1999 የአጠና ተራና 2000 ስላሴ ሳይት፣ በአዳማ በ1999 ሎጎና በ2000 ደምበላ ሳይት እና በባህር ዳር የ1999 ሳይት ሰባት እና የ2000 ማርያም ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ በይርጋለም ወኢ.ማ ሪል ስቴት፣ በሻሸመኔ ቤኬራ የንግድ ማዕከል፣ በአዋሳ የባህል ማዕከል፣ የስብሰባ አዳራሽ፣ የውሃ ሥራዎች ቢሮ፣ ኤች.አይ.ቪ. ሪሶርስ ማዕከልና ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ግንባታዎች ለአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴ ታስቦ የተሰራ ተዳፋት /Ramp/ እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ሲገልጹ፣ አሁን ስለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታ እንደተፈጠረ ማለትም በህንጻ አዋጁ በግልጽ እንደተመለከተና ወደ አፈፃፀም ሲገባ ከአዋጁ መጽደቅ በኋላ የተገነቡ የህዝብ መገልገያ ህንጻዎች በሙሉ ተደራሽ እንደሚሆኑ፣ ከአዋጁ መጽደቅ በፊትም የተገነቡት ቢሆኑ፣ ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ በመሥራት ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ለመፈራረም በዝግጅት ላይ ባለው የመግባቢያ ሰነድ አማካይነት ተደራሽ እንዲሆኑ ጥረት ይደረጋል ብለዋል፡፡

72. በመሆኑም የህዝብ መገልገያ ህንፃዎችና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታቸው የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ ታሳቢ አለማድረጉ ተገቢ ባለመሆኑ አዋጁ ወደ አፈፃፀም እንዲገባ ክትትል ቢደረግ መልካም ነው፡፡

የመስታወት ግድግዳ የሚገጠምላቸው ህንፃዎች መስታወቱ ደረጃውን የጠበቀና ጉዳት የማያስከትል ስለመሆኑ፣

73. የመስታወት ግድግዳ የሚገጠምላቸው ህንፃዎች መስታወቱ ደረጃ ሊወጣለትና ለተጠቃሚውም ሆነ ለሌሎች አካላት ጉዳት የማያስከትል መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል::

74. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩት በሻሸመኔ፣ በአዳማ፣ በአዋሳና በባህር ዳር ከተሞች በህንፃዎች ላይ የሚገጠሙ መስታወቶች ከውበት አንፃር እንጂ የአካባቢ ብክለት የማያስከትሉ (ሙቀት የማይፈጥሩና አንፀባራቂ) አለመሆናቸው በማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

75. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በግንቦት 2003 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የጸደቀው የህንጻ መመሪያ የፊት መስታወት ዓይነት(mirror glass) ወይንም ተመሳሳይ ውጤት እንዲኖረው የተደረገ መስታወት ለግንባታ የውጭ አካል አገልግሎት መጠቀም እንደማይቻልና በህንፃ ላይ ለሚገጠሙ የውጭ መስኮቶች አንፀባራቂነት የነዋሪውን ደህንነትና የትራፊክ እንቅስቃሴ የሚያውክ መሆን እንደሌለበት ቢገለጽም በአዳማ የግል ግንባታ ላይ ጭራሽ እንደማይሰራ፣ በሻሸመኔና በባህር ዳር ማዘጋጃ ቤት እንዲሁም በባህር ዳር ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት በመስተዋት ላይ እስከአሁን የተሰራ ሥራ እንደሌለ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

76. በሌላም በኩል አብዛኛው ሰው የመስተዋት ውበቱን እንጂ ምን አይነት መስታወት መጠቀም እንዳለበት የማያውቅና የተቀመጠ ዝርዝር መመሪያ (specification) የሌለ መሆኑን የኢትዮጵያ አማካሪ መሐንዲሶችና አርክቴክቶች ማህበር ኘሬዝዳንትና ፀሐፊ ገልጸዋል::

77. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስ የህንፃ መስተዋት መንፀባረቅ ብክለት (Glare pollution) ለሀገራችን ከተሞች አሳሳቢ መሆኑ እየተነገረ እንደሆነ፣ በዚህ ላይ መወሰድ ስላለበት የማስተካከያ እርምጃ በጥናት ላይ ተመርኩዘው እንደሚሠሩ፣ ለዚህም የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲን እንደሚያሳትፉ ዝርዝር የአሰራር ሥርዓቱን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በጥናት ላይ ተመርኩዘው እንደሚሰሩና ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጥበትና የህግ ማዕቀፍም እንደሚዘጋጅለት ገልጸዋል፡፡

78. በመሆኑም ከላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ለመረዳት እንደተቻለው ለህንፃ የሚገጠሙ መስታወቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶት አለመሰራቱን ያመለክታል።

መሪ ሰነዶች አስገዳጅ፣ ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩና የሚተገበሩ ስለመሆናቸው ፣

79. የጥራት ደረጃውን የጠበቀና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲኖር ለማስቻል የሚወጡት መሪ ሰነዶች አስገዳጅ፣ ተጠያቂነት ያላቸውና ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል::

80. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጠው በባህር ዳር በከተማ ልማትና ኢንዱስትሪ ቢሮ ቁጥጥር የሚገነባው የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የፕሬዝዳንት ቢሮ ለግንባታው የውጪ አካል የሚጠቀሙበት ከባህር ዛፍ አጣና የተሰራ መወጣጫ /scafholding/ ረጅም ጊዜ ፀሐይና ዝናብ ሲፈራረቅበት ስለበሰበሰ ሐምሌ 5 ቀን 2002 ዓ.ም መወጣጫው ፈርሶ ለ76 ሰዎች መውደቅና ከዚህም ውስጥ 20 ሰው የሞት 36 የከባድና በተቀሩት ላይ ቀላል ጉዳት ደርሷል፡፡

ፎቶ 5 በባህር ዳር ከተማ 76 ሰው የወደቀበትና 20 ሰው የሞት 36 የከባድና በቀሩት ላይ ቀላል አደጋ የደረሰበት የባህዳር ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ቢሮ ህንፃ ግንባታ የእንጨት መወጣጫ

81. እንዲሁም የሚካሄደው የቁፋሮ ስራ በአካባቢው ላይ የሚገኙትን ህንፃዎች፣ መንገዶችና እና ሌሎች የመሰረተ ልማት አውታሮችን የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግና በሚቆፈረው ቦታ አቅራቢያ የሚገኙ የህንፃዎች መሰረቶች ሊሸረሸሩ ይችላሉ ተብሎ ሲገመት የቁፋሮ ስራ በአጫጭር ክፍልፋዮች እንዲሰራ እና የህንፃዎቹ ግድግዳዎች በአስተማማኝ ሁኔታ መደገፍ ወይም መታሰር እንደሚኖርባቸው በህንጻ መመሪያው ላይ የተገለጸ ቢሆንም፣ በሻሸመኔ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ቁጥጥር ሥር የሚገነባው ቤኬራ የንግድ ማዕከል በአጐራባች ያለውን ህንፃ አስጠግቶ መሰረት ሲቆፍር የቤቱ መሠረት ከሥር በመቦርቦሩ የአጐራባቹ ህንፃ ላይ ስጋት የፈጠረ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ፎቶ 6 በሻሸመኔ ከተማ ቤኬራ የንግድ ማዕከል በግንባታ ወቅት ከወለል በታች ባለ ቁፋሮ በአጎራባቹ ያለውን G+2 ህንጻ ስጋት ላይ ጥሎት

82. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፣ የኮንስትራክሽን አካባቢ ደህንነት አጠባበቅ አዘጋጅተው ይህንንና ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ አደጋዎችን ለመከላከል እንደሚችሉ በማመን (Health and safety manual) ሠነዱ በውይይት ዳብሮ

የመጨረሻ ቅርፅ እንደያዘ፣ በባህር ዳር የደረሰውን አደጋ በተመለከተ ከኦዲቱ በደረሳቸው መረጃ መሠረት የመነሻ ጥናት እንዳደረጉ፣ የአደጋው ሥጋት አሁንም ሊኖር እንደሚችል በተጠቀሰው መሠረት ልዩ ጥንቃቄ እንዲወሰድ ከክልሉ ጋር አብረው እንደሚሰሩ፣ የሥራ ተቋራጮችም ሁሉንም የእንጨት መወጣጫዎች በብረት ለመቀየር የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ አቅም እስከሚያገኙ ሁለቱንም አቀላቅለው እንዲጠቀሙና ረጃጅም ህንጻዎችን በተመለከተ ግን የብረት መወጣጫ እንዲጠቀሙ እንደሚያደርጉ እንዲሁም በሻሸመኔ የታየው ችግር ለወደፊት እንዳይፈጠር በህንጻ አዋጁ ደንቡና መመሪያው ላይ በዝርዝር እንዳለ ገልጸዋል፡፡

83. ይህም በህንፃ መወጣጫ ላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መውጣት ያለበት አስገዳጅና ተጠያቂነትን የሚያጠናክር መመሪያ ቀደም ብሎ አለመውጣቱና ተዘጋጅቶ የተሰራጨውም መመሪያ በአጭር ጊዜ ወደ ትግበራ አለመገባቱ ለተከሰቱት ችግሮች እንደ አንዱ ምክንያት እንደሚሆን ይታመናል፡፡

በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የደህንነት መጠበቂያዎችን የሚጠቀሙ ስለመሆኑ፣

84. ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የደህንነት መጠበቂያዎችን ማሟላት ይገባቸዋል፡፡

85. ይሁን እንጂ የኦዲት ጉብኝት በተደረገባቸው የፌዴራልና የክልል ከተሞች በአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ሀዋሳ፣ ሻሸመኔ፣ አዳማና ባህር ዳር በሁሉም የግንባታ ሳይቶች የመኖሪያ ቤትና ህንፃ ግንባታ ሰራተኞች ለሥራ ሲሰማሩ የደህንነት መጠበቂያዎችን እንደማይጠቀሙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፎቶ 7 የደህንነት መጠበቂያ የማይጠቀሙ የግንባታ ሠራተኞች

86. በጉብኝቱ ወቅት የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በሻሸመኔ ማዘጋጃ ቤት መመሪያ ስለሌላቸው የደህንነት መጠበቂያዎችን እንዲያሟሉ ሠራተኞችን እንደማያስገድዱ፣ በአዳማ ማዘጋጃ ቤት ሰራተኛ የሚቀጥረው ኮንትራክተሩ እንደሆነና ሠራተኛውም ከሙቀት ጋር አያይዞ ያለመጠቀም ሁኔታ እንዳለ፣ በባህር ዳርም ያሉ የግንባታ ሠራተኞች እንደማይጠቀሙ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

87. የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ፣ የግንባታ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ መመሪያ ሠነድ አዘጋጅተው በሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ተሰጥቶ እንደተዘጋጀ፣ አሳትመው ሥራ ላይ እንዲውል እንደሚያደርጉና ስልጠናም እንደሚሰጡ፣ ይህንኑ ጉዳይ በዋናነት ከሚመለከተው ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በጋራ ለመስራት የጋራ የመግባቢያ ሰነድ ረቂቅ እንደተጠናቀቀም ገልጸዋል፡፡

88. ስለሆነም ያለው ጅምር ሥራ የሚበረታታ ቢሆንም፣ እስከአሁን ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት በግንባታው ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የደህንነት መጠበቂያዎች መጠቀማቸውን ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ብዛትና የማጠናቀቂያ ጊዜ በመርሐ ግብር ከተያዘው ጋር የሚጣጣም ስለመሆኑ፣

89. በክልልና ከተማ መስተዳድር በጀትና ድጋፍ የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ብዛት እና ጊዜ በመርሐ ግብር ከተያዘው ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ ከ1998 እስከ 2002 በፌዴራልና በክልል ከተሞች 396,000 ቤቶች ለመገንባት ታስቦ በዕቅድ ዘመኑ የተገነቡት ቤቶች ብዛት ግን 145,801 ሲሆን እንዲገነቡ ከታቀዱት 396 ሺህ ቤቶች አንፃር ሲታይ አፈፃፀሙ ከግማሽ በታች መሆኑን ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡



91. እንዲሁም በሻሸመኔ ግንባታቸው በ2000 ዓ.ም. እንዲጀምሩ የታቀዱት 26 ብሎኮች ሲሆኑ፣ በመጀመሪያው ፌዝ 4 ብሎኮች በሁለተኛው ፌዝ 9 ብሎኮች ሊጀመሩና ግንባታቸውም በስምንት ወር ውስጥ ሊጠናቀቅ ታቅዶ እስከ ጥቅምት 2004 ዓ.ም. ያልተጠናቀቁ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ፌዝ የተጀመሩት አራት ብሎኮች 82.39% መጠናቀቁና በሁለተኛው ፌዝ የተጀመሩት 9 ብሎኮች ደግሞ 92.91% የስትራክቸር ስራቸው ብቻ መጠናቀቁ፣

92. በአዋሳ በ2000 ዓ.ም 97 ብሎክ 92ቱ G+4፣ 5ቱ ደግሞ G+2 እንዲሰሩ የታቀዱ ሲሆን ወደ ክንውን የገቡት 75ቱ G+4ና 5ቱ G+2 እና የቀሩት 17 G+4 አለመጀመራቸው፣

93. በአዳማ በ2000 ዓ.ም ሊገነቡ ከታቀዱት 1,506 ቤቶች ውስጥ እየተገነቡ የሚገኙት 1,194 ቤቶች ሲሆኑ፣ ከነዚህም እስከ ጥቅምት 22/2004 ዓ.ም ድረስ 72.11 በመቶ የደረሱ ሲሆን 312 ቤቶች በደንበላ ሳይት በአርጂን/ጎርጅ/ እና ኮንትራክተር ሥራ ማቋረጥ ምክንያት ግንባታቸው መቆሙን የጽ/ቤቱ አፈፃፀም ሪፖርት መግለጹ፣

94. እንደዚሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ የቤቶች የማጠናቀቂያ ጊዜ እቅድና አፈጻጸም የተጣጣመ ስለመሆኑ ሲታይ፡- በ2000 በጀት ዓመት ሊገነቡ የታቀዱ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በኦሮሚያ 14,313፣ በአማራ 13,214፣ በደቡብ 6,355፣ በትግራይ 5,548፣ በሐረር 1,540ና በድሬዳዋ 1,877 ሲሆን በቅደም ተከተል አፈፃፀማቸው ግን እስከ ሐምሌ 2003 ዓ.ም. ድረስ 58%፣ 72%፣ 70%፣ 69%፣ 70%ና 79% መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. ለዚህም ምክንያቱ በአዲስ አበባ፣ በአዋሳ፣ በአዳማ፣ በሻሸመኔና በይርጋለም የሚገኙ የየከተሞቹ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው ከግብዓት እጥረት (ሲሚንቶ፣ ብረት፣ የሳኒተሪና የኤሌክትሪክ እቃዎች)፣ የተቋራጭ የአቅም ውስንነት፣ የመሠረተ ልማት አቅራቢ ድርጅቶች የሥራ መጓተት እና የበጀት እጥረት ማጋጠሙን የገለጹ ሲሆን፣ በሲሚንቶና በአርማታ ብረት እጥረት ምክንያት ፕሮጀክቶቹ እየተጓተቱ መሆኑንም ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የ2004 የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

96. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በ2000 ዓ.ም. የተጀመረው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ የግብዓት አቅርቦት ችግር በዋናነት የሚጠቀስ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

97. ይሁን እንጂ የተጠቀሱትን ችግሮች ቀደም ብሎ በማሰብ ለመፍታት ወይም ለመቀነስ የተደረገ የስጋት ትንተና (risk analysis) ግምገማ ያልተደረገበት በመሆኑ የቀረቡት ምክንያቶች ተገቢ መስለው ቢታዩም፣ የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ብዛት በመርሐ ግብሩ ከተመለከተው ጋር የማይጣጣሙ መሆኑ፣ የአፈጻጸሙ ጊዜ በተራዘመ ቁጥር

ለግብዓት ዋጋ ንረት እንዲጋለጥ፣ ተገልጋዩም ህብረተሰብ የመግዛት አቅሙ እንዲቀንስና እንዲያገኝ የሚፈለገው ግልጋሎት እንዲራዘም ሊያደርገው ይችላል፡፡ ስለሆነም የጋራ መኖሪያ ቤቶች መርሀ-ግብር ሲዘጋጅ በቅድሚያ የሚያጋጥሙ ችግሮች ታስበባቸው የሚከሰቱ ችግሮች እንዲቀንሱ ማደረግ ቢቻልም አፈጻጸም ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ሥጋቶች ሊወገዱ የሚችሉበት ሁኔታ በጥናቱ (risk manage) ሊካተቱ በተገባ ነበር፡፡

የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ሥራ ጎን ለጎን የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ስለመከናወኑ፣

98. የግንባታ ስራ በሚከናወንበት ቦታ ጎን ለጎን የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ሊኖር ይገባል::

99. ነገር ግን በሻሸመኔ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ጐን ለጐን እንደማይከናወንና ለመብራት ኃይል ብር 2,567,997.74 /ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ከሰባ አራት ሳንቲም/ ከፍለው ትራንስፎርመር የለም በመባሉ እስካሁን መብራት ያልገባላቸው ሳይቶች እንዳሉ፣ ውሃም ላይ እንደዚሁ ችግር እንዳለና መሠረተ ልማቱን ለማከናወን የበጀት እጥረት እንዳጋጠመ እንዲሁም በሀዋሳ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከመብራት ኃይል አቅርቦት ጋር በተያያዘ የትራንስፎርመር እጥረት በማጋጠሙ መብራት ያላገኑ ብሎኮች እንዳሉ፣ በአዳማ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የመብራት መሥመር ዝርጋታ በሚፈለገው ጊዜና ፍጥነት እንደማይሠራና በአዲስ አበባ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በሚያከናውኑ የባለድርሻ አካላት ጋር ያለመናበብና የትራንስፎርመር ችግር እንዳለ የየከተሞች የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

100. እንዲሁም በአዋሳ ደቡብ ስድስት ሳይት የሚገኙትን 345 ቤቶች ለቤት ባለቤቶች የተላለፈና ለሳይቱ የተሟላ የመብራት አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ጥረት የተደረገ ቢሆንም፣ ከሚያስፈልገው ትራንስፎርመር ውስጥ በመብራት ሀይል በኩል የቀረበው ለዘጠኝ ብሎኮች ብቻ ነው፡፡ ለቀሪዎች አሥራ ስድስት ብሎኮች የሚያስፈልጉ ሁለት ትራንስፎርመሮች ማቅረብ ባለመቻላቸው በሳይቱ የተሟላ የመብራት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ አለመቻሉንና የመብራት ትራንስፎርመር ለማስገባት ለመብራት ኃይል ክፍያ የተፈጸመው ከአመታት በፊት ቢሆንም መሥሪያ ቤቱ የትራንስፎርመር

እጥረት እንዳለበት በመግለጽ ማቅረብ አለመቻሉ ከሀዋሳ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

101. በተጨማሪም በ1999ና በ2000 ዓ.ም. በክልሎችና በአዲስ አበባ የተገነቡ ቤቶች በ2003 ሐምሌ የመብራት አገልግሎት ያልተሟላላቸው ቤቶችን እንዲሟላላቸው ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማዕከልና በክልል ክትትል እየተደረገ ቢሆንም፣ አሁንም በሚፈለገው ወቅት ለማሟላት ያልተቻለበት ሁኔታ እንደሚታይ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2003 ዓ.ም አፈጻጸም ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡



በ1999 የተጀመሩ ግንባታዎች ትራንስፎርመር አቅርቦት ነሐሴ 2003 ዓ.ም



በ1999 የተጀመሩ ግንባታዎች የቆጣሪ አቅርቦት ነሐሴ 2003 ዓ.ም

102. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ፣ የመብራት ኃይል አቅርቦትን በተመለከተ በናሙና የተገኘው ግኝት ትክክል እንደሆነና ችግሩን ለመቅረፍ ከብረታ ብረትና ሜትስ ኮርፖሬሽን ከመብራት ኃይል እና ውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በጋራ አብረው እየሠሩ እንደሆነና የቆጣሪ፣ የትራንስፎርመርና የኤሌክትሪክ ገመድ አቅርቦት ችግር እንዳለ ገልጸዋል፡፡

103. ይህ አሠራር ቤቶችን በወቅቱ ለማስተላለፍ ችግር ከመፍጠሩም በላይ ተገልጋዩ ህብረተሰብ የተሟላ የመሠረተ ልማት አገልግሎት እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

በአንድ ቦታ ላይ በርከት ብለው የሚገነቡ ህንጻዎች የዝናብ ውሃ መሰብሰብ የሚችሉ (water harvesting) ሆነው ስለመሠራታቸው፣

104. በአንድ ቦታ ላይ በርከት ብለው የሚገነቡ ህንጻዎች (ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮንደሚኒየም ቤቶች፣ ከፍተኛ ህንፃዎች. . .) ዲዛይን ከመልካም ተሞክሮዎች በመማር የዝናብ ውሃ መሰብሰብ የሚችል (water harvesting) ሆነው መሠራት አለባቸው፡፡

105. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት እንደታየው፣ የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችና ከፍተኛ ህንፃዎች ግንባታቸው የዝናብ ውሃ መሰብሰብ የሚችሉ ሆነው አልተሰሩም፡፡

106. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ እስከአሁን ባለው አሠራር እንደሌለና ሊኖር ግን እንደሚገባው ገልጸዋል፡፡

107. በአንድ ቦታ ላይ በርከት ብለው የሚገነቡ ህንጻዎች (ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮንደሚኒየም ቤቶች፣ ከፍተኛ ህንፃዎች. . .) ዲዛይን ከመልካም ተሞክሮዎች በመማር የዝናብ ውሃ መሰብሰብ (water harvesting) የሚችል ሆኖ ቢሰራ መልካም ነው፡፡

ምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ሲገነቡ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና የማምለጫ አመላካቾች አለመዘጋጀታቸው፣

108. ምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ሲገነቡ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና የማምለጫ አመላካቾች በግልጽ ቦታ የሚታዩ፣ እና አለም አቀፍ ምልክቶችን የሚጠቁሙ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡

109. ሆኖም በምድብ "ሐ" ስር ለሚገኙ ህንፃዎች የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና ማምለጫ ደረጃዎች በሻሸመኔ ማዘጋጃ ቤት መመሪያ ስለሌለ እንደማያስገድዱ እንዲሁም በባህር ዳር ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ መኖር እንዳለበት በአዋጅ የተቀመጠ ቢሆንም እስካሁን በአለው አሰራር እንደማይረጋገጥ ከኃላፊዎቹ ለማወቅ ተችሏል፡፡

110. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፣ የአደጋ ጊዜ ማምለጫ ደረጃዎችና ማስጠንቀቂያ በተመለከተ ክልሎች በራሳቸው ሊያወጡት የሚችሉት ጉዳይ ቢሆንም፣ በአገር አቀፍ የእሳት አደጋ መከላከያ ኮድ ዝግጅት እንደተጠናቀቀና ፀድቆ ሥራ ላይ በሚውል ወቅት ችግሩ የሚፈታ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

111. በመሆኑም በምድብ "ሐ" ስር ለሚገኙ ህንፃዎች ጉዳዩ በሚመለከታቸው ኃላፊዎች የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና ማምለጫ ደረጃዎች ትኩረት ተሰጥቶ አለመሰራቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳቦች

112. ኮዶች፣ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች ስለመኖራቸው፣ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ስለመዳረሳቸው፣ ስለመተግበራቸውና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ስለመከናወናቸው ለማጣራት ኦዲት ተደርጎ በዝርዝር የኦዲት ግኝቶች ላይ የተመለከቱት ጉልህ የሆኑ የአሠራር እና የአፈፃፀም ችግሮች ታይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተዘጋጅቶ የጸደቀው የህንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አፈፃፀምን በተመለከተ የተሰጠውን የግንዛቤ ማስጨበጫ የወሰዱ በፌዴራልና በክልል የሚገኙ የአመራሮች ከታች ላሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት አለማስተላለፋቸው፣
- የጸደቀው የህንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልደረሳቸው በክልል ከተሞች የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት መኖራቸው፣
- መመሪያው በደረሳቸው የክልል ከተሞች በክልሉ ቋንቋ ተተርጉሞና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ አለመቅረቡ፣
- የህንፃ አዋጁ፣ ደንብና መመሪያው በደረሰበት የክልል ከተሞች እስከ አሁን ወደ ትግበራ አለመገባቱ፣
- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙትን ሰነዶች ማወቅና ማግኘት የሚፈልጉ ባለሙያዎች (ባለድርሻ አካላት) ሰነዶቹን በቀላሉ ሊያውቁና ሊያገኙ የሚችሉበት የመረጃ ሥርዓት በቂ አለመሆኑና መለቀቅ ያለባቸው በሙሉ በድረ-ገጽ አለመለቀቃቸው፣

113. በክልልና የከተማ መስተዳድሮች ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች የመነሻ ጥናት መኖሩን፣ ግንባታውም ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ተገቢው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን፣ የስራ ክንውኑም በተያዘለት የጊዜ ገደብና የቤት ብዛት

መሆኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን ለማጣራት ኦዲት ተደርጎ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

- በቂ የመነሻ ጥናት ሳይደረግ የተገነቡ የህንጻና የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች መኖራቸው፣
- በመንግስትም ሆነ በግለሰብ ለሚገነቡ ህንፃዎች ወይም መኖሪያ ቤቶች ለግንባታ ከተፈቀደላቸው ቦታ ምን ያህሉን ለአረንጓዴ ሽፋን መጠቀም እንደሚገባቸው የሚገልፅ ስትራቴጂክ እንደየከተሞቹ ነባራዊ ሁኔታ አለመዘጋጀቱ፣
- የአማካሪ ባለሙያ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች እና ትልልቅ የግለሰብ ህንፃዎች መኖራቸው፣
- በግንባታው ቦታ ሊቀመጥ የሚገባው የመረጃ መዝገብ (site book) የማይቀመጥባቸው የግለሰብና የመንግሥት ህንፃዎች መኖራቸው፣
- በጋራ መኖሪያ ቤት፣ በመንግሥትና በግለሰብ ህንፃዎች በግንባታ ሂደት ሊደረግ የሚገባው የግንባታ ግብዓት የናሙና ፍተሻ የማይደረግባቸው ግንባታዎች መኖራቸው፣
- የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ ታሳቢ የማያደርጉ የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንፃዎች መኖራቸው፣
- ለህንፃዎች የሚገጠሙ መስታወቶች ከውበት አንፃር እንጂ የአካባቢ ብክለት የሚያስከትሉ (ሙቀት የሚፈጥሩና አንፀባራቂ) መሆናቸው ላይ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ አለመሆኑ፣
- የመኖሪያ ቤትና ህንፃ ግንባታ ሰራተኞች ለስራ ሲሰማሩ የደህንነት መጠበቂያዎችን የማይጠቀሙ መሆኑ፣
- ሊገነቡ የታቀዱ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ብዛትና የማጠናቀቂያ ጊዜ ከአፈጻጸሙ ጋር የተጣጣመ አለመሆኑ፣
- የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ያልተሟላባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች መኖራቸው፣
- በአንድ ቦታ ላይ በርከት ብለው የሚገነቡ ህንጻዎች (ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮንደሚኒየም ቤቶች፣ ከፍተኛ ህንፃዎች. . .) ዲዛይንና ግንባታ የዝናብ ውሃ መሰብሰብ (water harvesting) የሚችል ሆኖ አለመሰራቱ፣
- የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና የማምለጫ ደረጃዎች የሌላቸው በምድብ "ሐ" ስር የሚገኙ ግንባታዎች መኖራቸው፣

114. በአጠቃላይ የህንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተዘጋጅቶ በግንቦት 2003 የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁንና በመኖሪያ ቤትና ህንጻ ግንባታ ዙሪያ ለተሰማሩ አስፈፃሚ አካላት ስለአፈጻጸሙ ግንዛቤውን እንዲያገኙና ሰነዱም እንዲደርሳቸው የሚደረግበት ሥርዓት ካልተዘረጋና በአፋጣኝ ወደ ትግበራ ካልተገባ፣ ግንባታዎች ከመገንባታቸው በፊት በቂ የመነሻ ጥናት ካልተደረገ እንዲሁም የመኖሪያ ቤትና ህንጻ ግንባታ በሂደት ላይ እያለ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ስራ ካልተሰራ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ሥራ ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያርሙና በአጠቃላይ ግንባታዎች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

115. ኮዶች፣ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች መኖራቸውን፣ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት መዳረሳቸውን፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሠራታቸውንና መተግበራቸውን በተመለከተ፣

- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተዘጋጅቶ በጸደቀው የህንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ላይ የሚፈጠረውን የአተረጓጎምና የአፈፃፀም ችግር ለማስወገድ በፌዴራልና በክልል የሚገኙ ግንዛቤውን ያገኙ የበላይ አካላት የወሰዱትን የግንዛቤ ማስጨበጫ ከታች ላሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሁሉ የሚያወርዱበት መድረክ ሊመቻች፣ ይህም የሠራተኛ ፍልሰትን በማገናዘብ በድግግሞሽ የሚሰጥ ሊሆንና፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም በቤት ልማት የሚሳተፉ አካላት ሁሉ ስለ ሰነዱ አተገባበር ሊያውቁ የሚችሉበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል፡፡ የተዘጋጁትም ሰነዶች በሁሉም አስፈጻሚ አካላት እጅ መድረሳቸው ሊረጋገጥ፣ ሰነዶቹን ማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማግኘት የሚችልበት መንገድ ሊመቻችለት /በድረ-ገጽ ሊለቀቅ፣ ቤተ መፃህፍት ሊቀመጥ፣ ለገበያ ሊቀርብ…/ እናበተሰራጩባቸው ክልሎችም ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ ሊቀርብ እንዲሁም በግንባታው ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የህንፃ መመሪያው በቶሎ ሊተገበር፣ አፈፃሙም ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙትን ሰነዶች በሙሉ ማወቅና ማግኘት የሚፈልጉ ባለሙያዎች (ባለድርሻ አካላት) ሰነዶቹን በቀላሉ ሊያውቁ የሚችሉበት የሰነዶቹን ዝርዝር የሚገለጽና ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ የሚያስረዳ የመረጃ ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በበቂ ሁኔታ መዘርጋት አለበት፡፡

116. በክልልና ከተማ መስተዳድሮች ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች የመነሻ ጥናት መኖሩን፣ ግንባታውም ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ተገቢው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን፣ የስራ ክንውኑም በተያዘለት የጊዜ ገደብና የቤት ብዛት መሆኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን በተመለከተ፣

- ለግንባታዎች በጀት ከመመደቡና ወደ ትግበራ ከመገባቱ በፊት ስለሚገነቡበት ቦታና አካባቢ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዋጪነት በቂ ጥናት መደረግ አለበት፣ ጥናቱ ሲደረግ ተሣታፊ የሚሆኑ ባለድርሻ አካላት በዝርዝር ተለይተው ሊታወቁና ኃላፊነታቸው ሊገለጽ ይገባል፡፡
- ለአረንጓዴ ሽፋን ተብለው የሚተው ቦታዎች እንዲኖሩ በሚመለከታቸው አካላት ታሳቢ ሊደረጉ፣ ለዚሁ ጉዳይ ተከልለው የተያዙ ቦታዎችም በአግባቡ ሊለሙና አስፈላጊው ጥበቃና ክብካቤ ሊደረግላቸው፣ ኀብረተሰቡም በዚህ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል መድረክ ሊዘጋጅለት፣ የህንፃ ግንባታ የሚያካሂዱ አካላትም ዲዛይኑ ከመጽደቁ በፊት ለአረንጓዴ ሽፋን የተተወ ቦታ መኖሩ ሊረጋገጥ እና በዲዛይኑ መሠረት እንዲተገበር ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የመኖሪያ ቤትና የህንፃ ግንባታ እንዲኖር በግንባታው ሂደት ውስጥ አማካሪ ባለሙያ በቂ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ አማካሪ ባለሙያውም በሥራው ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል በቂ ክህሎት ያለው መሆኑ በሥራ አፈጻጸሙ ሊለካ እንዲሁም በየጊዜው በሚሰጡ የክህሎት ማሻሻያ ስልጠናዎች የሚሳተፍ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ አማካሪ ባለሙያ በግንባታ ሂደት ያጋጠመውን የግንባታ ሂደት ችግሮች የመረጃ መዝገብ (site book) ላይ ሊያሰፍር፣ ትእዛዝ ሊሰጥና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡
- የህዝብ መገልገያ ህንፃዎችና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዲዛይን ሲጸድቅ የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ ታሳቢ ማድረጉ ታይቶ እንዲጸድቅ ሊደረግና ስለተግባራዊነቱም ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡
- ለህንፃዎች ስለሚገጠሙ መስታወቶች ዝርዝር ጥናት ተጠንቶ ደረጃ ሊወጣላቸውና ወደ አገር ውስጥም ሲገቡ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ከውጭ በሚገቡትን የመስታወት ምርቶች ፋንታ በአገራችን ምርት መጠቀም የሚቻልበት ሁኔታም ሊፈጠርና የግንባታ ባለቤቶች ዲዛይን ሲያጸድቁ ሊጠቀሙበት ያሰቡት የመስተዋት አይነት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸው ታይቶ ዲዛይኑ እንዲጸድቅላቸውና አፈፃፀሙም ላይ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

- የሥራ ተቋራጮች የሙያ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የደህንነት መጠበቂያዎችን ማሟላት እንደ አንድ መስፈርት ሆኖ ሊቀመጥና ሊተገበር ይገባል። የግንባታ ሠራተኞችም የተዘጋጀላቸውን የደህንነት መጠበቂያ መጠቀማቸው በክትትል መረጋገጥ አለበት።
- በግንባታ ሂደት ሊደረግ የሚገባው የግንባታ ግብዓት የናሙና ፍተሻ ሳይደረግ ግንባታዎች እንዳይከናወኑ በሚመለከታቸው የቤት ልማት አስፈፃሚ አካላት በቂ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡
- የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እንዲኖሩ በግንባታ ዙሪያ በተለያየ የሙያ ዘርፍ የሰለጠኑና ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች በሥራው ላይ ሊሰማሩ፣ አፈፃፀማቸውም እየተገመገመ በየጊዜው የክህሎት ማሻሻያ ስልጠና ሊሰጣቸው፣ በአስፈጻሚ አካላት የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር ሊኖር፣ ጥሩ አፈፃፀም ላላቸው ማበረታቻ ሊሰጥና የግንባታ ግብዓት የናሙና ፍተሻ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ዕቅድና አፈፃፀሙ የተጣጣመ እንዲሆን የሥራ ተቋራጮች የተሰጣቸውን ሥራ በወቅቱ እንዲያጠናቅቁ የሚገቡት ውል አስገዳጅ ሊሆን፣ የግብዓት አቅርቦትን ችግር ለመፍታትና ከቤት ማስተላለፉም በኋላ ህብረተሰቡ የተሟላ አገልግሎት እንዲያገኝ ከግብዓት አቅራቢዎችና የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ከሚያከናውኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡
- በአንድ ቦታ ላይ በርከት ብለው የሚገነቡ ህንጻዎች (ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮንደሚኒየም ቤቶች፣ ከፍተኛ ህንፃዎች. . .) ዲዛይንና ግንባታ የዝናብ ውሃ መሰብሰብ የሚችሉ ሆነው ቢሰሩ ለተለያየ አገልግሎት በመጠቀም የውሃ እጥረትን ለመቀነስ ያስችላል፡፡
- በምድብ "ሐ" ስር የሚገኙ ግንባታዎች ዲዛይን ሲጸድቁ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና የማምለጫ ደረጃዎች እንዳላቸው ታይቶ ሊጸድቅና አፈጻጸሙም ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት፣ እንዲሁም መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

የኦዲት መገምገሚያ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

ኦዲት ተደራጊ፣ <u>የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር</u>

የኦዲት አካባቢ፣ <u>የህንፃና የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ደረጃና ቁጥጥር</u>

የኦዲት ጭብጦች **Audit Issues**	**የኦዲቱ መስፈርቶች** **Evaluative Criteria**
1. ኮዶች፣ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች ስለመኖራቸው፣ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ስለመዳረሳቸው፣ ስለመተግበራቸውና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ስለመከናወናቸው ማጣራት፣	
1.1 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚመራባቸውና ለግንባታ ስራ መለኪያ የሚሆኑ መሪ ሰነዶች (ኮዶች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች)፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች መኖራቸውን፣ እና መሰራጨታቸውን ማጣራት፣	1 ለግንባታ ለሚውሉ ግብዓቶች መደረግ ስላለበት የናሙና ምርመራ ዝርዝር መመሪያ መዘጋጀትና መሰራጨት አለበት::
	2 መሪ ሰነዶች የማስፈጸሚያ ህጎችና ደንቦች የስራ አፈፃፀም መለኪያ ሆነው ሊዘጋጁና ለስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ሊሰራጩ ይገባል፡፡

የኦዲት ጭብጦች **Audit Issues**	የኦዲቱ መስፈርቶች **Evaluative Criteria**
	3 የመኖሪያ ቤትም ሆነ ህንጻ የሚገነቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች የግንባታ ህጎችንና ደንቦችን በቀላሉ የሚያገኙበት ሥርዓት መኖር አለበት::
	4 የሙያ ማህበራት አባላቱ የሚመሩበት የስነ-ምግባር ደንብ ሊያዘጋጁና ሊያሰራጩ ይገባል::
	5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ፍቃድ ለሚሰጣቸው አካላት የሥነ ምግባር ደንብ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
	6 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራበት ስትራቴጂክ እቅድ ሊኖረው ይገባል::
	7 እያንዳንዱ ክፍል ከስትራቴጂክ ዕቅድ ተነስቶ አመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በዕቅዱ መሠረት ሊያከናውን ይገባል፡፡
1.2. ለአስፈጻሚ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሠራታቸውንና ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ማጣራት፣	8 ለአስፈጻሚ አካላት ስለመሪ ሰነዶች የማስፈጸሚያ ህጎችና ደንቦች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
	9 የተሰራጩት የማስፈጸሚያ ህጎችና ደንቦች አፈፃፀማቸው የሚገመገምበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል::
	10 የሙያ ማህበራት ያወጡትን የሥነ ምግባር ደንብ አባላቱ እየተገበሩት መሆኑ የሚረጋገጥበት የክትትል ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
	11 መሪ ሰነዶች በየስንት ጊዜው መከለስ እንዳለባቸው የጊዜ ገደብ ሊወሰንና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል::

የኦዲት ጭብጦች **Audit Issues**	የኦዲቱ መስፈርቶች **Evaluative Criteria**
2. በፌዴራል መንግስት በጀትና ድጋፍ በፌዴራልና በክልል ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች የመነሻ ጥናት መኖሩን፣ ግንባታውም ደረጃውን የጠበቀ ለመሆኑ ተገቢው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን፣ የስራ ክንውኑም በተያዘለት ጊዜና የገንዘብ መጠን መሆኑንና አላማውን ስኬታማ ማድረጉን ማጣራት፣	
2.1 በፌዴራል መንግስት በጀትና ድጋፍ ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች የመነሻ ጥናት መኖሩንና ግንባታውም በጥናቱ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ፣	12 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተማ ነዋሪዉን አቅም ያገናዘበ የመኖሪያ ቤት እና ህንጻ ለመገንባት የሚያስችል አቅጣጫ አመላካች የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ማቅረብ አለበት::
	13 በፌዴራል መንግስት በጀትና ድጋፍ ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች ከመገንባታቸው በፊት የመነሻ ጥናት ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	14 እያንዳንዱ ከተማ ለመኖሪያ ቤቶችና ህንጻ ግንባታ የቅድሚያ ጥናት ሰነድ ሊኖረውና ከአገር አቀፍ ጥናትና እቅድ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መኖር አለበት::

የኦዲት ጭብጦች **Audit Issues**	የኦዲቱ መስፈርቶች **Evaluative Criteria**
2.2 በፌዴራልና በክልል የሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ስራ መኖሩን ማረጋገጥ፣	15 ለግንባታ ተቆጣጣሪነት የሚመደበው ባለሙያ ማሟላት የሚገባው መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	16 የመኖሪያ ቤትም ሆነ የህንፃ ግንባታ ከተፈቀደለት ቦታ ላይ ለአረንጓዴ ሽፋን ለሚሆን ስፍራ መመሪያ መኖር አለበት:: ለተፈፃሚነቱም የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	17 የግንባታ ህግ በሚተላለፉ አካላት ላይ ውሳኔ የሚሰጥ አካል ሊሰየምና ውሳኔ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ ተወስኖ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	18 በግንባታ አማካሪዎች ተሳታፊነት መሰራት ስላለባቸው የመኖሪያ ቤቶች እና ሕንፃዎች ደረጃ ለይቶ የሚያሳይ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	19 ግንባታ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው የግንባታ ስራ በሚያከናወንበት ቦታ የግንባታ ክትትል የመረጃ መዝገብ ሊያዘጋጅ እና የግንባታ ተቆጣጣሪውም ክትትል በሚያደርግበት ወቅት ያገኘዉን መረጃ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ ሊያሰፍር ይገባል፡፡

የኦዲት ጭብጦች **Audit Issues**	የኦዲቱ መስፈርቶች **Evaluative Criteria**
	20 በግንባታ ወቅት ለወቅታዊ ክትትልና ድጋፍ እንዲያመች በተመዘገበ ባለሙያ የተዘጋጀ ዲዛይንና የስራ ዝርዝር እንዲሁም የግንባታ ፍቃድና "ለቁጥጥር አገልግሎት ብቻ የሚያገለግል" የሚል ማህተም ያረፈበት የጸደቀ ፕላን ኮፒ በግንባታ ሳይት ላይ መገኘት ይኖርበታል::
	21 የቤትና ህንፃ ግንባታ እንደ የምድባቸው ኘላን ሲሰራ መሟላት የሚገባው መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
	22 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት በጀት ለሚሰሩ ህንጻዎች የግንባታ ውሎችን ማዘጋጀትና ተፈፃሚነቱን መከታተል ይኖርበታል፡፡
	23 ማንኛውም ግንባታ ከመከናወኑ በፊት የግብዓት ጥራት የናሙና ፍተሻ መደረግና ዉጤቱ በፅሁፍ ተዘጋጅቶና ማህተም ሰፍሮበት መቅረብ አለበት::
	24 የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንፃዎች ሲገነቡ ለአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴ የሚያመቹ መሆናቸዉ መረጋገጥ አለበት::
	25 ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ሲገነቡ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና የማምለጫ አመላካቾች በግልጽ ቦታ የሚታዩ፣ እና አለም አቀፍ ምልክቶችን የሚጠቁሙ

የኦዲት ጭብጦች **Audit Issues**	የኦዲቱ መስፈርቶች **Evaluative Criteria**
	ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
	26 የመስታወት ግድግዳ የሚገጠምላቸዉ ህንፃዎች መሥተዋቱ ደረጃ ሊወጣለትና ለተጠቃሚውም ሆነ ለሌሎች አካላት ጉዳት የማያስከትል መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል::
	27 የጥራት ደረጃውን የጠበቀና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲኖር ለማስቻል የሚወጡት መሪ ሰነዶች አስገዳጅና ተጠያቂነት ያላቸውና ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል::
	28 የግንባታ ህጎች ተፈፃሚ መሆናቸው ክትትል የሚደረግበት የሪፖርት ቅፅ (Format) ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡
	29 ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ የተገነቡ የመኖሪያ ቤቶችና ህንጻዎች የፍሳሽ ማቆያ (ማከማቻ) ሊኖራቸው ለዚህም መስፈርትና ደረጃ ሊዘጋጅ እና ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡
	30 ከተሞች፣ አዳዲስ የመኖሪያ ስፍራዎችና የህንጻ መስሪያ አካባቢዎች የጎርፍ ውሀ ማስወገጃ መስመር ሊኖራቸውና የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ አለበት፡፡
	31 ከግንባታ ጋር በተያያዘ በቁፋሮ የሚወጣ አፈር፣ ድንጋይ እና የግንባታ ፍርስራሽ በግንባታው አካባቢ ሲከማች እና ከግንባታው ቦታ ወደ ሌላ ሥፍራ

የኦዲት ጭብጦች Audit Issues	የኦዲቱ መስፈርቶች Evaluative Criteria
	ሲጓጓዝ ነዋሪውን ሕብረተሰብ የማይጎዳ፣ አካባቢን የማይበክል እና የተቆፈረውም ጉድጓድ ለደህንነት የማያሰጋ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
	32 በአንድ ቦታ ላይ በርከት ብለው የሚገነቡ ህንጻዎች (ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮንደሚኒየም ቤቶች፣ ከፍተኛ ህንፃዎች. . .) ዲዛይን የዝናብ ውሃ መሰብሰብ የሚችል ሆኖ መሰራቱን ማጣራት፣
	33 ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የደህንነት መጠበቂያዎችን ማሟላት ይገባቸዋል፡፡
	34 ተራራማና ኮረብታማ በሆኑ የከተማ ቦታዎች ለግንባታ ስራ የሚውለው የተዳፋትነት መጠን (Slope) ሊወሰንና መመሪያ ሊዘጋጅለት፣ ተፈጻሚነቱም የሚረጋገጥበት የቁጥጥር ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
	35 በአማካሪነት ሙያ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	36 በመንግስት የከተማ ልማት መ/ቤቶች፣ ማዘጋጃ ቤቶችና የክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ዘርፎች ውስጥ ተቀጣሪ ለሆኑ ሠራተኞች የአማካሪ ባለሙያ

የኦዲት ጭብጦች Audit Issues	የኦዲቱ መስፈርቶች Evaluative Criteria
	ፈቃድ መሰጠት የለበትም፡፡
2.3. በፌዴራልና በክልል ታቅደው የሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች በተፈለገው ስፍራ በተያዘላቸው ጊዜና የገንዘብ መጠን ተጠናቀው ለተገነቡበት አላማ እየዋሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣	37 ለመኖሪያ ቤትና የህንጻ ግንባታ ወጪን ለመቀነስ የሚያስችል የግንባታ ቴክኖሎጂ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚ የሚሆንበት ስርዓት መኖር አለበት፡፡
	38 ሚ/ር መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል የሚገነቡ የመንግስት ህንፃዎች በተያዘላቸዉ ጊዜ እንዲጠናቀቁ የዲዛይን፣የግንባታ አስተዳደርና የግብዓት አቅርቦት ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡
	39 ግንባታ እንዲያከናውኑ የተፈቀደላቸው አካላት የግልና የድርጅቶች ሕንጻዎችንና መኖሪያ ቤቶችን በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እንዳለባቸው መመሪያ ሊዘጋጅና ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል፡፡
	40 የመኖሪያ ቤቶች ልማት እና የመንግሥት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ ለከተማ ነዋሪዉ ጥራቱን የጠበቀ፣ በሚፈልገዉ ጊዜና መጠን እንዲሁም በተመጣጣኝ ወጪ የተገነባ ቤት ለማቅረብ እንዲቻል የወጪ ቆጣቢ ዲዛይን፣ የቴክኖሎጂ አማራጮች፣ የግንባታ ግብዓት አቅርቦት፣ የአቅም ግንባታ እና የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ሊሰራ ይገባል፡፡

የኦዲት ጭብጦች Audit Issues	የኦዲቱ መስፈርቶች Evaluative Criteria
	41 በፌዴራል መንግሥት በጀትና ድጋፍ የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ብዛት፣ ስፋት እና ጊዜ በመርሐ ግብር ከተያዘው ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡
	42 የግንባታ ስራ በሚከናወንበት ቦታ ጎን ለጎን የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ሊኖር ይገባል::
	43 ለመኖሪያ ቤቶችና ህንጻ ግንባታ የመሬት አጠቃቀም ስልት ሊዘጋጅና ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡ የመሬት አጠቃቀም ስልቱም የደን (እጽዋት) ሽፋንን የማያስተጓጉልና ለምነት ያላቸውን የእርሻ መሬቶች አገልግሎት የማያደናቅፍና የመሰረተ ልማት ወጪን የሚቀንስና የጉዞ ርቀትን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡
	44 የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃ ግንባታ በየከተሞቹ በተዘጋጀው ደረጃና በተቀመጠው መመሪያ መሰረት የቦታ ደረጃቸውን (1ኛ ደረጃ ቦታ፣ 2ኛ ደረጃ ቦታ፣ …) ጠብቀው የተገነቡ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መኖር አለበት::
	45 የሐይማኖት ተቋማት የሚገነቡበት የቦታ ስፋት፣ ስፍራ እና የቦታ ደረጃን በሚመለከት መመሪያ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

የኦዲት ጭብጦች Audit Issues	የኦዲቱ መስፈርቶች Evaluative Criteria
	46 ትምህርት ቤቶች የሚገነቡበት የቦታ ደረጃና ስፍራ መመሪያ ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም መመሪያ ተፈጻሚነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	47 የመኖሪያ ስፍራዎችና ሌሎች ዘርፎች (የቢሮ፣ የንግድ፣ የኢንዱስትሪ ወዘተ) የሚገነቡበት የዞን ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆንበት አሰራር ሊመቻች ይገባል::
	48 በአንድ አካባቢ ለሚገነቡ መኖሪያ ቤቶችና ህንፃዎች ሊኖራቸው ስለሚገባው ዲዛይን፣ ቁመት፣ ቀለም …..(uniformity) መመሪያና ደንብ መኖር አለበት፡፡
3. ከመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፣ የመረጃ ባንክ መኖሩንና የአያያዝና የጥንቅር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ማጣራት፣	
3.1 ሚ/ር መ/ቤቱ ከመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃ ግንባታ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፣	49 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል ከሚገኙ የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር ይገባል::

የኦዲት ጭብጦች Audit Issues	የኦዲቱ መስፈርቶች Evaluative Criteria
	50 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህንፃ ግንባታ ላይ በተለያየ ሙያ የተሰማሩ ባለሙያዎችንና የባለድርሻ አካላትን አቀራርቦ የሚያወያይ መድረክ ማመቻቸት ይኖርበታል::
3.2 በሚ/ር መ/ቤቱ ለቤቶችና ህንፃ ግንባታ አገልግሎት የሚውል የመረጃ ባንክ መኖሩንና እና የመረጃ ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፣	51 በተለያዩ አካላትና የምርምር ተቋማት የተከናወኑ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ዉጤቶች ሊሰባሰቡና ሊጠናቀሩ ይገባል፡፡
	52 ጥናቶቹም ኢኮኖሚያዊ አዋጪነታቸዉ ተረጋግጦ የቤት ልማት ተሳታፊ ለሆኑ ለመንግስትም ሆነ ለግል ዘርፍ የቤት ልማት ተሳታፊ አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል::
	53 በግንባታ ሂደት የተገኙ በጎ ተሞክሮዎችን እንደገና ለመጠቀምና ደካማ ጎኖች እንዳይደገሙ ለማድረግ በክትትል ወቅት የተገኙ መረጃዎች የሚሰባሰቡበት፣የሚጠናቀሩበትና በመረጃነት የሚጠበቁበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል::

አባሪ 2

1.2 የአሠራር ፍሰት መግለጫ (Process Description)

የኮንስትራክሽንና ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሰው ሃይል ልማት እና የደረጃዎች ዝግጅት የሥራ ሂደት

የስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ባለሙያዎች እና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ የስራ ሂደት



አባሪ 2.1

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሕግ ማስፈፀም የሥራ ሂደት ጥናት

ፍላጎት ደሰሳ
- የቀረበ ጥያቄ
- ከክትትል ግምገማ የተለየ ክፍተት

↓

የህግ ማስፈፀሚያ ስርዓት ቀረፃ
- የክትትል ስርዓት
- የማስፈፀሚያ ስርዓት

↓

አቅም ግንባታ
- ቴክኒካል ድጋፍ
- የማስፈፀሚያ ስርዓት ሰነዶች ማስተዋወቅ ፣መሰራጨት

↓

ክትትልና ቁጥጥር
- የማስፈፀሚያ ስርዓት ሰነዶች አፈፃፀም
- የወጡ ህጎችና ደረጃዎች አፈፃፀም
- የአቅም ግንባታ ስራዎች አፈፃፀም

↓

- በተዘጋጁ ማስፈፀሚያ ስርዓቶች የአቅም ግንባታ፣ ክትትልና ቁጥጥር የተደረገላቸው አካላት

የኮንስትራክሽን ግብዓትና ቴክኖሎጂ ምርምር የሥራ ሂደት ጥናት

የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ፍላጎት/ጥያቄ

↓

የኮንስትራክሽን ግብዓትና ቴክኖሎጂ ምርምር እቅድ (ቅድመ ምርመር)

↓

የኮንስትራክሽን ግብዓትና ቴክኖሎጂ ምርምር ፕሮጀክት

↓

የኮንስትራክሽን ግብዓትና ቴክኖሎጂ የማላመድ ፕሮጀክት(ማላመድ)

↓

የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ምርምር ስርፀት

↓

በአዲስ ግብዓቶች እና ቴክኖሎጂዎች የታገዘ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ

አባሪ 2.2

የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግሥት ህንፃዎች ቢሮ

አዲስ የመኖሪያ ቤቶች ልማት ክትትልና ድጋፍ የስራ ሂደት

1. የመኖሪያ ቤት ፍላጎት/ ጥናት/
2. ጥናትና ምርምር
3. የቤት ፋይናንስ
4. ሎጂስቲክስና አቅርቦት
5. አቅም ግንባታ
6. ክትትልና ግምገማ

የመንግስት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ክትትልና ድጋፍ የስራ ሂደት

1. የመንግስት ህንጻ ግንባታ ፍላጎት/ጥያቄ
2. የዲዛይን ድጋፍ ስራ
   - የፕሮጀክት ፕሮግራም ዝግጅት
   - የዲዛይን ፕሮግራም ቀረፃ
   - የበጀት ዝግጅት
   - የዲዛይን አማካሪ መረጣ
   - ኮንስትራክሽን መረጃ ዝግጅት
3. የግንባታ አስተዳደር ድጋፍ ስራ
   - የቅድመ ኮንስትራክሽን ሰነድ ግምገማ
   - የግንባታ ቴክኒክ ድጋፍ
4. የክትትል ድጋፍ ስራ
5. ግንባታዉ የተጠናቀቀ የመንግስት ተቋም